# ህወሓት/ኢህአዴግ እና እኛ

## (ትዝብት፣ ወቀሳ እና ምክር)

ካሳ ኃይሉ (ዶ/ር)

የዚህ ፅሁፍ ዋና ዋና መልዕክት የሚከተሉት ናቸው

1. ባለፉት ጥቂት ዓመታት እየተከሰቱ ያሉ ሕዝባዊ አንቅስቃሴዎች የ 27 ዓመታት ግፍና ጭቆና ዉጤቶች ሲሆኑ አስካሁን እየተደረገ የነበረው ሰለማዊ ትግል ፍሬ አልባ በመሆኑ ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው!
2. ልክ እንደ ከዚህ ቀደሙ ባሁኑ ወቅት እየደረሰ ላለዉ የሰዉ ነፍስና የንብረት ጥፋት ተጠያቂው ከህወሓት/ኢህአዴግ ዉጪ ማንም ሊሆን አይችልም!
3. ይህ ስርአት እስካሁን ይህችን ታላቅ አገር መቀለጃ እንዲያረጋት ያስቻሉት ህወሓት/ኢህአዴግ የኢትዮጲያን ህዝብና አንድነት ለመናድ ከፋሽስት ኢጣልያ ተዉሶ የተጠቀመዉን በቋንቋ ላይ የተመሰረት እና ምንም ታሪካዊ መሠረት የሌለዉን ብሄር ብሄረሰብ የሚል የመሃይም እና የጋጠ ወጦች ፅንሰ ሃሳብ ትክክል እንደሆን አምነዉ የተቀበሉ ሰዎች ናቸዉ!
4. ህወሓት/ኢህአዴግን እንደ ታቦት ማየት ለደጋፊዎቹም ሆነ ለጠላቶቹ ምንም ፋይዳ የሌለው ቅዠት ነዉ!
5. ህወሓት/ኢህአዴግ ያረጀ እና ኋላ ቀር አመለካከቱንና መሪዎቹን ማስወገድና የኢትዮጲያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ የቀሩት ሁለት ብቸኛ አማራጮች ናቸው!
6. ህወሓት/ኢህአዴግ ልቦና ገዝቶ በድንቁርና ከፈጠረዉና ለ40 አመታት ይዞት ከተጓዘው ቅጥ ያጣ ጎጠኝነትና ከአጉል ትዕቢት ራሱን ማፅዳት አለበት፡፡ ይህ ባይሆን ግን ጥቂቶችን የጠቀመዉ ይህ አገዛዝ አርሱ የኔ ናቸዉ ያላቸዉ ግን ምንም ያልፈየደላቸዉ ኢትዮጵያዉያን ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ ከመሆን አያያመልጡም!

በቂ ጊዜ ላላችሁ መልዕክቴን ዘርዘር አድርጌ እንዳቀርብ ፍቀዱልኝ

፩. የሐረርጌ ገበሬ "ሃጃ ኒቀለቲ መሌ ሂንጪቱ" ይላል። ዕዉነት ትቀጥናለች እንጂ አትበጠስም ለማለት ነዉ። ምንም እንኳን በሃገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት 27 ዓመታት ትርጉም በሌለዉ ባልበሰለና እና የተዉሶ በሆነ የፖለቲካ ፍልስፍና ምክንያት የንፁሃን ነፍስ ሲቀጠፍ ብዞዎቻችን እንዳልሰማና እንዳላየ ብንሆንም አሁን አገሪቱ ወደ እማትመለስበት ደረጃ የደረሰችና የኛም ዝምታ ጊዜው ያለፈበት ይመስለኛል። በግልፅ እንደሚታየዉ አሁን አሁን እንደ አዲስ ጉዳዩ ያገባኛል የሚለዉና ተቆርቋሪ ነኝ ባዩ እየበዛ ይመስላል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ሲቋቋም ጀምሮ መሰረታዊ የዓላማ ችግር የነበረበት የጥሬ ጎረምሶች ስብስብ ነበር። ይህ ስብስብ ከነማርክስ አስተምህሮ በመነሳት የኮሚንዝም ጠላት የሆነዉን ካፒታሊዝም ዋና ጠላት አድርጎ ይነሳል። ከዚሁ የበለጠ ደግሞ የፋሽስት ጣሊያን - ከኢትዮጵያ ጋር በተገናኘ - ቁልፍ ጠላቶች የሆኑትን አፄ ሚኒልክን፣ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን እና ጣሊያን "አማራ" ብሎ የሚጠራዉን (የህወሓት እና የጣሊያን ትርጉም እጅጉን ቢለያይም) ሕዝብ የትግራይ ህዝብ (ውክልና ባይኖረዉም) እና የህወሓት ቀንደኛ ጠላት አድርጎ ይነሳል። ይህ ከድንቁርና ዉጪ ሌላ መገለጫ ሊሰጠዉ የሚችል አይመስለኝም። ይህ የተዛባ መነሻዉና ዓላማዉ በኢትዮጵያ ሕዝብ መስዋእትነትና በደርግ የላሸቀ አገዛዝ ታግዞ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ከኢትዮጵያ ታሪክ እና ባህል ጋር ምንም ዝምድና በሌለዉ መልኩ ኢትዮጵያዉያንን በቋንቋቸው ምክንያት "ጨቋኝ" እና "ተጨቋኝ" በሚል እንዲከፋፍል አስቻለዉ። ጨቋኝ የተባሉ ንፁህ ኢትዮጵያዉያን እንደከብት ታረዱ። እንደቁሻሻ ከነ ነፍሳቸው ገደል ተጨመሩ። እናቶች አዉራ ጎዳና ላይ ቆመዉ ጡታቸው እንዲቆረጥ ተደረገ። ለህወሓት/ኢህአዴግ ባለስልጣናትና ተለጣፊዎች ሲባል ሚሊዮኖች የሳት አራት ተደረጉ። ነፍሰ ጡሮች ሆዳቸው ተተለተለ። በባህረ ነጋሽ (ኤርትራ) እና ትግራይ ያሉ ወገኖቹን ከጣሊያን ባርነት ለማዉጣት በግሩ ከሶስት እስከ ስድስት ወራት ተጉዞ ነፍሱን የሰዋዉ ወታደር ነፈጠኛ የሚል ቅፅል ተለጥፎበት የታሪክ በቀል እንዲያርፍበት ተደረገ። ኧረ ስንቱ።

ይህም ሆኖ ግን ይህ እጅግ የሚገርም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለዉ ሕዝብ ተዉ ግድ የላችሁም ሕዝብ ይታረቅ፣ አብሮ ይኑር ተዉ አትለያዩን ቢል ከጀሮ ይልቅ የዓዕምሮ ድንቁርና ይከፋልና ህወሓት ጆሮዬ ጥጥ ነዉ ብሎ አምቢ አለ። ስማቸው ለፅሁፍ የማይበቃ ተቃዋሚ ነን ባይ ፖለቲከኞች ሳይቀር ‘ተዉ ይህን ብሔር ብሔር የምትሉትን ተዉ ጦሱን አትችሉትም’ ብለዉ ሲመክሩ ታዝበን አልፈናል። ይህ ሁሉ ድካም ግን ምንም መፍትሄ ሳያመጣ 27 ዓመት ሞላን። የእስከ ዛሬው ግድያ እንዳልታየ ታልፎ ይሁን፣

የእስከ ዛሬው ግፍና መከራ እንዳልተሰማ ታስቦ ይሁን፣ ካሁን በፊት የሞቱት የተንገላቱት ቋንቋቸው ዝቅ ያለ ይሁን፣ ወይም ሌላ ምክንያት ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት እየደረሱ ያሉ ጉዳቶች ህወሓት/ኢህአዴግንና ተቆርቋሪዎቹን በተለየ መልኩ በጣም እንዳሳሰቡ ይታያል። ያሁኑ ክስተት ድንገት የተከሰተ ነው ወይም ከሌላ የቡድን እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት አለዉ ብሎ የሚያስብ ወይ አያዉቅም ወይ ደሞ ያዉ ድንጋይ ራስ ሆዳም ነዉ። ሰላማዊ የትግል መንገዶችን ሁሉ ጥርቅም አድርጎ የዘጋዉ ህወሓት/ኢህአዴግ ነዉ። ሃሳብ በነፃነት እንዳይንሸራሸር በሕግ ነፃ የዜና ምንጮችን አና ነፃ ጋዜጠኝነትን ያጠፋዉ ህወሓት/ኢህአዴግ ነዉ። ሰዎች በችሎታቸው ሳይሆን በተወለዱበት ቤተሰብ ወይም ጎጥ ወይ ደሞ በሚናገሩት ቋንቋ ምክንያት ኑሮ ተራራ ሲሆንባቸው ከዚያም አልፎ እኖር ብለዉ በየበረሃዉ ሲታረዱ ኢትዮጵያዊነታቸዉን የተጠራጠረዉ ህወሓት/ኢህአዴግ ነዉ። ባልመረጠዉና ሊቀይረዉ በማይችለዉ የትዉልድ ቀየው ወይም ወላጆቹና ቋንቋዉ ምክንያት መኖር ያልቻለ ኢትዮጵያዊ ከዚህ በላይ እንዲታገስ ተጠብቆ ከሆነ እዉነትም ይህች አገር ተረግማለች። አሁን እየሆን ያለዉ ከዚህም በሁዋላ የሚሆነው ህወሓት/ኢህአዴግ ሌላው ኢትዮጵያዊ እርስ በርሱ ሲባላ እኔ ለብቻ እጠቅመዋለሁ ወይም እለየዋለሁ ያለውን ሕዝብ ትልቅ አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑ ለሁላችንም ግልፅ ሊሆን ይገባል። ለዚህ ማነዉ ተጠያቂዉ?

፪. ህወሓት/ኢህአዴግ በዚህች አገር ዉስጥ ባለፉት 27 ዓመታት ለደረሰውና ወደፊትም ለሚደርሰዉ የኢትዮጵያዉያን የእርስበርስ ግጭት እና የአገሪቱ ሉዓላዊነት መደፈር ዋና ተጠያቂ እንደሆነ ለማንም ጤነኛ ሰዉ ግልፅ ነዉ። ይህን በቀላሉ ለመገንዘብ በሃገራችን ኢትዮጵያ ቅድመ ህወሓት እና በዘመነ ህወሓት የተከሰቱ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ኩነቶችን አለፍ አለፍ ብሎ ማየት ይበቃል። ህወኃት/ኢህአዴግ ሁሉንም ነገር ጠላት ወይም ወዳጅ አድርጎ ነው የሚመለከተው። በርግጥ ጠላቶቹን ወዳጅ ለማድረግ የሥነልቦና ዝግጅት ባይኖረውም ወዳጆቹን ጠላት ለማድረግ ግን ቅንጣት የማያመነታ አሳዛኝና አሳፈሪ ድርጅት ነው። ገና በለጋ እድሜው አብረው ለመታገል ሲደራደሩ የነበሩ የሱ ቢጤ ድርጅቶችን ራት አብልቶ በተኙበት በማረድ አረመኔነቱን ያሳየ ድርጅት ነው። የደርግ ውድቀት እየቀረበ ሲመጣ ላነገበው ኋላቀርና ጎጠኛ አመለካከት/ዓላማ ይጠቅመኛል ያለውን አንጋፋውን የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን ወደ ዕቅፉ  አምጥቶ የሚፈልገዉን ካገኘ በኋላ እንደ አሮጌ ካልሲ አጉል ቦታና አጉል ሰዓት ላይ ወርውሮ የጣለ ድርጅት ነው። በኢትዮጵያ ሕዝብ ያላሰለሰ ጥረትና በኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ደጋፍ እንዲሁም በደርግ በራሱ ዝርክርክነት ምክንያት ህወኃት ሃገሪቱን ሲቆጣጠር ብዙ የተደከመበትን በኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት፣ በሌላት አቅም አገሪቱ ደክማ ያፈራችውን የተማረ ሃይል፣ እና አገሪቱ በዘመናት ጉዞ የገነባቻቸዉን ቁልፍ ታሪካዊ እና ወታደራዊ ተቋማት በጠላትነት በመፈረጅ ይህችን አገር የማፍረስ ሥራውን ጀመረ። ምንም እንኳን ይህ በጠላትነት የተፈረጀ የህብረተብ ክፍል እና ተቋም ወዲያውኑ ራሱን ለመከላከል ያደረገው ጥረት ባይኖርም እያደር ወደሚያመረቅዝ ቁሥልነት አልተለወጠም ማለት ግን የዋህነት ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን ህወሃት/ኢህአዴግ ጭልጥ ወዳለ የታሪክ ብረዛ እና የህዝብ ፍረጃ ገባ። የጣሊያን ፋሽስቶች ግልጽ በሆኑ ምክንያቶች አጼ ሚኒሊክን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን፣ እና አማራ የሚሉትን ህዝብ ዋና ጠላት አድርገው  ኖረዋል። ለጣሊያኖች ኢትዮጵያን እንዳይገዙ እንቅፋት የሆኑባቸውን አካላት ሁሉ እንደ ጠላት መቁጠር ማንም የማይደነቅበት ነው። ለህወሃት/ኢህአዴግ ግን የነዚህ ጠላትነት ለሁሉም ሰው ግልፅ ላይሆን ይችላል። የህወሃት እና የሻዕቢያ መስራቾች ወላጆቻቸዉና አያቶቻቸው በጣሊያን ባንዳነት ኢትዮጵያን እና ለኢትዮጵያ ክብር የቆሙትን ሁሉ እንደጠላት እያዩ ያደጉ ናቸው። እነዚህ የባንዳ ልጆች የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያዉቁት የጣሊያን ፋሽስት ባስተማረው መልኩ ነው። ለነዚህ ጉዶች አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሃንስ፣ ራስ አሉላ አባነጋ፣ ባልቻ አባ ነፍሶ፣ ራስ መኮንን፣ እቴጌ መነን፣ ፊታውራሪ ገበየሁ፣ በላይ ዘለቀ፣ ሃይለማርያም ማሞ፣ ፊታውራሪ ሃ/ጊዮርጊስ፣ ዘርዓይ ደረስ፣ አብርሃም ደቦጭ፣ ሞገስ አስገዶም እና እልፍ አእላፍ ጀግኖች ለነሱ ጠላት ናቸው። ምክንያቱም የጣሊያን ፋሽስት ጠላት የነርሱም ጠላት ነውና። በርግጥ ሰብሃት ነጋ የተባለው በዕድሜ ከፍ ያለው ጉድ ጣሊያን ከአማራ የባሰ ምን አደረገን ሲል በአደባባይ ተናግሯል። ጣሊያንን የወጋ አማራ ብቻ ነው ከሚል ብሽቅ አረዳድ ተነስቶም ቢሆን የተናገረው መልዕክቱ ግልፅ ነው።

የነእርሱ ጀግኖች ሃይለስላሴ ጉግሳን የመሳሰሉ ለጣሊያን ያደሩና ይችን ትልቅ አገራቸውን የካዱና ያዋረዱ ፈሪዎች ናቸው። የፈሪ ልጅ ፈሪ ነው። በግፍ ወህኒ የወረወሩት ወጣቱ እንዱአለም አራጌ ባንድ ወቅት የኢህአዴግ ጭካኔ የሚመነጨው ከፍርሃት ነው ሲል ሰምቻለሁ። በጣም ትክክል ነው። ህወሃት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊ ጀግንነት በደማቸው ውስጥ ባለ ሰዎች የተገነባ አይደለም። ልክ እንደ አብዛኛው የጣሊያን ጌቶቻቸው በሌብነት ዝሙትና ጋጠወጥነት የተካኑ ፈሪዎች ስብስብ ነው።

የአፄ ሚኒሊክ ጠላትነትም በጣሊያን ፋሽስቶች ተይዞ በባርነት ሲማቅቅ የነበረውን የትግራይ እና ቢሳካላቸው ኖሮ የባህረ ነጋሽን (ኤርትራን) ህዝብ ለመታደግ እስካፍንጫው የታጠቀውን የጣሊያን ጦር ለወራት በእግራቸው ተጉዘዉ

አሳፍረው መመለሳቸው እና ሕዝቡን በነፃነት እና በኩራት እንዲኖር ማድረጋቸው ነው። ያም ሆነ ይህ ጣሊያን ጌቶቻቸውን ያዋረደ ሰው እንዴት የነእሱ (የህወሃት/ኢህአዴግ) ወዳጅ ይሆናል?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክን ጠላትነትም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው። የህወኃት ጥላቻ እንዴት ለኛ ጌቶች (ጣሊያኖች) የኢትዮጵያ ህዝብ እንዳይገዛ ትገዝታለች ከሚል የመጣ ነው። እነ አቡነ ጴጥሮስ እና ሌሎች ጀግና እና ፃድቅ አባቶች ይመሯት የነበረችው ቤተ ክ/ን በዘመኑ የከፈለችውን መስዋዕትነት የታሪክ ትምህርት ከፋሽት ጣሊያን ወይም ከባንዳዎች ለተማረ ሰው ሊገባው አይችልም። ቤተ ክርስትያኗን እና ነፍጠኛ የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ ትርጉም በጭራሽ ሳያውቁ የኦርቶዶክስ ቤ/ን የነፍጠኛ መሳባሰቢያ ነች ብለው የሚለፍፉ አንጋሬዎች አይተናል። ይሁን። ሌላው የህወሃት ጠላት 'አማራ' እየተባለ የሚጠራው ህዝብ ነው። በጣሊያን ወረራ ዘመን አማራ የሚለው ስም ክርስቲያን የሆነውን የወሎ፣ ጎጃም፣ ሸዋ፣ እና ጎንደር ህዝብ እንዲወክል ተብሎ የተፈጠረ ጽንሰ ሃሳብ ነው። ጣሊያን ይህን ያደረገበት ዋና ምክንያት የሃይማኖት ጭቆና አለ በሚል በደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ የሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታዬችን ከክርስቲያኑ ወገናቸው ለመለየት ነበር። ጣሊያኖች ያላወቁት ወይም ያልገባቸው ነገር የኢትዮጵያ ክርስትናና እስልምና ሃይማኖቶች በሚገርም መስተጋብር ተደጋግፈውና ተከባብረው የሚኖሩ መሆናቸውን ነው። ጣሊያን አማራ የሚለውን ህዝብ ጠላት ያደረገበት ዋና ምክንያት ግን በኤርትራም ሆነ በትግራይ ያላጋጠመውን ፈተና ከላይ በጠቀስኳቸው አካባቢዎች የሚኖረው ህዝብ እጥፍ ድርብ አድርጎ ስላደረሰበት ነው። የጣሊያን ጥላቻ የመነጨው ከሃይማኖቱ ወይም ከቋንቋው አልነበረም። ይልቁንም ከህዝቡ አልገዛ ባይነት እና ጀግንነት የተነሳ ነበር። ህወሃት/ኢህአዴግ ምንም እንኳ ጣሊያን አማራ ብሎ የከለለውን ያህል ግዛት መከለል ባይፈልግም የጠላትነት አድማሱን ግን በጣም አስፍቶታል። ይህ ሕዝብ ጀግንነቱ እና ሃይማኖቱ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው፣ በባህሉ፣ በአካባቢው፣ እና በታሪኩ የተነሳ የጥላቻ እና የቂም በቀል (ለጣሊያን ጌቶቻቸው ሲሉ) ግፍ ላለፉት 27 ዓመታት ሲቀበል ኖሯል። ግልጽ በሆነ አድሎአዊ አሰራር አማራ ተብሎ ሚጠራው ህዝብ እንዳይማር፣ የጤና አገልግሎት እንዳያገኝ፣ የተበላሹ መድሃኒቶች እና ምግቦች እንዲጠቀም፣ ሃብት እንዳያፈራ፣ እና ባልመረጠዉ ስብዕናው ምክንያት ተሸማቆ እና አፍሮ እንዲኖር ተደርጓል።

ይህ መጠነ ሰፊ የታሪክ ብረዛ በህወሃት/ኢህአዴግ ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚሠራ ሥራ ነው ። አማራ የሚሉትን ህዝብ እንደሚፈሩት በራሳቸው አንደበት ተናግረዋል። ይህ ግን ከጣሊያን ጌቶቻቸው የተማሩት እንጂ አሁን አማራ ብለው የጠሉት ህዝብ በውጭ ወራሪ ስር ሲወድቁ ነፃ አዉጥቶ፣ ተርበው ቢሰደዱ አንገታቸዉን ቀና አድርጎ አብልቶ አጠጥቶ፣ ፈጣሪ አግዟቸው መግዛት ሲችሉ ከለም መሬቱ ላይ ያመረተውን ሽጦ እስከ ዛሬ ያቆያቸዉ ህዝብ ነው። ይህን ህዝብ የትግራይ ህዝብ ጠላት ሊልበት የሚችልበት ምንም ምክንያት የለም። ጥቂት የባንዳ ልጆች ከተማሩት ሽፋፋ ታሪክ ተነስተው የፈጠሩት ተረት ተረት እንደሆነ ግልጽ ነው።

ህወሃት/ኢህአዴግ ክልል ብሎ  ኢትዮጵያን በከፋፈለበት ወቅት ምንም ታሪካዊ መሠረት በሌለው ሁኔታ ባህረ ነጋሽን ጣሊያን ባወጣለት ስም ሸልሞ ለሻዕቢያ እጅ መንሻ ከማድረጉ ባሻገር አማራ ብሎ የሚጠራው ህዝብ እርሻ አርሶ የትግራይን ህዝብ ይታደግባቸው የነበሩ የጎንደርና የወሎ መሬቶችን ትግራይ ክልል ዉስጥ በማስገባት ለአፈሩና ለውሃው ያለውን ቅናትና ፍቅር ሲያሳይ መሬታቸውን ለወሰደባቸው ሰዎች ያለውን ጥላቻ በሄሊኮፕተር ሳይቀር እየደበደበ ዛሬም እያሳየን ነው።

የህወሃት/ኢህአዴግ የክልል አከላለል ቀመር ሲጀመር ጀምሮ የእንቧይ ካብን ያህል ጥንካሬ የለውም። ከግለሰብ ይልቅ ቡድን ላይ የሚያተኩረው የደንቆሮ ፖለቲካ አንድን ቡድን ትግሬ ወይም አማራ ብሎ ይጠራል። አንድ ግለሰብ ግን ትግሬ ወይም አማራ ለመሆን ምን ምን ማሟላት እንዳለበት አይታወቅም። አሁን ባለው አሠራር እንኳን ከሁለትና ከሶስት ብሄር ተወለድኩ የሚሉ ሰዎች ብሄርህን ምረጥ ሲባሉ ይውላሉ። ምንም እንኳ ይህ የህወሃት ቀመር የተዛባ ቢሆንም አማራ የሚሉት ህዝብ ላይ ያላቸው ጥላቻ ግን ክልል አመሰራረት ላይ በግልጽ ወጥቷል። ኢትዮጵያን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሁሉ የህዝቧ አሠፋፈር ምን ያህል የተሰባጠረና በጭራሽ ቋንቋን ወይም ባህልን የተከተለ እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ትግራይ ውስጥ በርካታ ጎሳዎች ተሰባጥረው ይኖራሉ። ጎጃም፣ ጎንደር፣ ወሎ፣ ሸዋ፣ ወለጋ፣ ሐረርጌ፣ ኢሉባቡር፣ ከፋ፣ ጋሞ ጎፋ፣ ሲዳሞ እንዲሁም ባሌ በርካታ ጎሳዎች - የተለያዩ ቋንቋ ባህል ያላቸው - እደሚኖሩባቸው ይታወቃል።

በነመለስ ዜናዊ ጥላቻን መሠረት ያደረገ ድንቁርና ምክንያት የአማራን ህዝብ አናሳ ለማድረግ የተለየ ቋንቋ ያላቸው ሁሉ እየተፈለጉ ልዩ ዞን ተፈጠርላቸው። በአንፃሩ በትግራይ እና ለጊዜው መጠቀሚያ ማድረግ የፈለጉትንና ኦሮሞ ብለው የጠሩትን ህዝብ የሚወክለው ክልል በጭራሽ ሌላ ጎሳ፣ ቋንቋ፣ እና ባህል እንደሌለባቸዉ ተደርገዉ ተቋቋሙ። ወሎን፣ ጎጃምን፣ ጎንደርንና ሸዋን ለመበጣጠስ ምክንያት ያላጣው ህወሃት  ትግራይን ለማስፋፋትና አብዛኛውን ሃረርጌን የሶማሌ ብቻ ብሎ ለመከለልም አልተቸገረም። ህዝብን የሚያክል ነገር መጠቀሚያ አደርጋለሁ ብሎ የተነሳ ቀመር የትም ማድረስ እንዳልቻለ ይኸው አሁን ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው።

በርግጥ 27 ዓመት ሙሉ በኦሮሞ ህዝብ ስም በሶማሌ ህዝብ ስም የዚህች አገር ሃብት አልተዘረፈም ማለት አይቻልም። ለህወሃት አባላትና አቃጣሪዎች ብቻ የተፈቀደ ኮንትሮባንድ ንግድ አሁን ድረስ ልክ እንደ ህጋዊ ሥራ በሶማሌ እና ኦሮሚያ ክልሎች እየተከናወነ ይገኛል። አንድ ሰዉ አገር ወስጥ የገዛዉ ሸቀጥ ኮንትሮባንድ የሚሆንበት አገር ይቺው የኛው ጉድ ብትሆንም ለህወሃት ግን ይህ ትልቅ የገቢ ምንጭ ነው። አንድ ዜጋ ፎጣ ገዝቶ ከሐረር ወደ አደስ አበባ ሲመጣ ከተገኘ በጉሙሩክ ይዘረፋል። አንድ የህወሃት ወታደር ወይም አቃጣሪ ግን ግድግዳ የሚያክል ቴሌቪዥን አውቶብስ ላይ ጭኖ ያልፋል።

አይናቸዉን በጨው ያጠቡት እነዚህ ገብጋባ የህወሃት ሌቦች በሁሉም ክልሎች በከርሰ ምድር ካላ ማዕድን (ሁመራ ጎንደር) እና መሬት (ጋምቤላ) እስከ ባንክ ቤት ውስጥ እስከተቆለፈበት የአገሪቱ የወርቅ ክምችት (በብሔራዊ ባንክ) ድረስ በመዝረፍ አገሪቷን ራቁቷን እንዳስቀሯት ይታወቃል።

ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ከሌለው የዘራፊ እና የባንዳ አምላኪ ቡድን ከዚህ የተለየ ምንም አይጠበቅ ይሆናል። ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ግፍና መከራ የኢትዮጵያን ህዝብ ገፍቶ አሁን የደረሰበት ደረጃ አድርሶታል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ንፁህ ኢትዮጵያዊያን በህወሃት ዋልጌ ፖለቲካ ምክንያት ህይወታቸውን አጥተዋል። ሆን ተብሎ ትውልድን ለማጥፋት በተቀረፀ የጤናና የትምህርት ፖሊሲ ምክንያት ሰርተው መብላት እንዳይችሉ ተደርገዋል። ሚሊዮኖች የማንነት ቀውስ ውስጥ ገብተው ራሳቸውን እና አገራቸው እንዲጠሉ ተደርገዋል። ሚሊዮኖች ሆን ተብሎ ንብረት አልባ ሆነው በድህነት እንዲማቅቁ ተደርገዋል። ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል የግፉ ዝርዝር ረጅም ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ከ 'እግዚአብሄር በታች መንግስት ነው ያለኝ' ብሎ የሚያስብ በመሆኑ ከዛሬ ነገ ይህ መንግስት ዞር ብሎ ያየኝ ይሆናል፣ ኑሮየን ይለውጥልኝ ይሆናል እያለ ይኸው 27 ዓመት ሞላው። ዉስጣቸው ወይም ከጎናቸው የቆሙ አስተዋይ ሰዎች ብዙ ጊዜ ለመምከር ሞከሩ ግን አልተሳካም።

'ከዚህ ወርቅ ከሆነ ህዝብ በመፈጠሬ እኮራለሁ" በሚል ደነዝ የሚመራ ድርጅት ምናልባት የአዋቂዎችን ምክር እንዲሰማ አይጠበቅ ይሆናል። ትዕቢት ወድቀትን ትቀድማለችና ጀሮአቸውም ልባቸውም በትዕቢት ደንቁሮ ይኸው የሮምን አወዳደቅ ሊወድቁ ነው። እኔ የሚያሳዝነኝ በነእሱ ጦስ አብሮ አፈር የሚለብሰው ምስኪኑ ኢትዮጵያዊ ነው። ይህ በጥንቃቄ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል። ያም ሆነ ይህ ይህች አገር እና ህዝቧ ላሳለፉትና እያሳለፉ ላሉት ሰፊ አድማስ ያለው ስቃይና መከራ ተጠያቂ የሚሆን ከህወሃት/ኢህአዴግ ውጭ ፈልጎ ማግኘት አይቻልም። የህወሃት ፈጣሪ የሆነውን ሻዕቢያ ወይም ህወሃት የፈጠረውን (ምክንያት ሆኖ) ግንባት 7 ወይም ሌላ ለመውቀስ መሞከር ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነው። ህወሃትን ማንም አይነካበትም። ማንም አይጋራውም።

፫. ህወሃት/ኢህአዴግ በስልጣን ላይ ለመቆየት በጥንቃቄ አዘጋጅቶ የተጠቀመበት ፅንሠ ሃሳብ ቢኖሮ 'የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የራስን መብት በራስ መወሰን እስከመገንጠል' የሚል ግንጥል አስተምህሮ ነው። ይህ ፅንሰ ሃሳብ ጆሴፍ ስታሊን የሶቭየት ህብረትን ለመመስረት እንደ ዋነኛ ማሳመኛ የተጠቀመበት ነው። ስታሊን ግን ኔሽን (Nation) ሲል በወቅቱ ራሳቸውን የቻሉ አገሮችን ለምሳሌ ዩክሬይን ወይም ጆርጂያን እንዲሁም ናሽናሊቲ ("Nationality) ሲል ደግሞ የነዚህን አገሮች ዜጎች ማለቱ ነበር። በአስራ ዘጠኝ ስድሳዎቹ የማርክሲዝም ሌኒንዝምን ፍልስፍና በቅጡ ሳይመረምሩ እንደቀኖና ሲያነበንቡ የነበሩ እንደዋለልኝ አይነት ያልበሰሉ ተማሪዎች ይህን የስታሊን አስተምህሮ ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ማጣጣም አስፈልጓቸዉ ኖሮ አማራ፣ ትግሬ ወዘተ ኔሽን (Nation) እንደሚባሉ ወይም ሊባሉ እንደሚችሉ ጭልም ያለ ትምህርት አስተማሩ። የሚያሳዝነው እነዋለልኝም ሆነ የሱን ጥራዝ ነጠቅ ዲስኩር ይዘው ወደ ሻዕቢያ ጉያ የሮጡት እነ ለገሠ (መለስ) ዜናዊ አማራ ወይም ትግሬ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሳይነግሩን ይኸው 27 ዓመት ሞላን። ምንም እንኳን እነለገሠ ጫካ ሲደርሱ ትግሬውን ከጨቋኝነት ወደ ተጨቋኝነት ቢያወርዱትም ዋለልኝ ጨቋኝ ናቸዉ ያለው አማራዉንና ትግሬውን ነበር። የመጨረሻ ደሃ የሆነን ሕዝብ አንዲህ ባለ ቅጥ ባጣ መልኩ ታሪካዊ ጫና ዉስጥ መክተት መሃይምነት ምን ያህል ከፉ ነገር እንደሆነ ያሳያል።

የሚሰማ ጆሮ ያለው የለም እንጂ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ላለፉት 30 ዓመታት ሲናገሩ የነበረውን መልሼ በራሴ አማርኛ እጽፈዋለሁ። ካበላሸሁ ይቅር ይበሉኝ ጌታዬ። 'ብሔር' የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ከግዕዝ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም 'አገር' ማለት ነው። ስለዚህ ለስታሊን ኔሽን (Nation) ለሚለው ቃል አቻ ትርጉም ተደርጎ ሊወሰድ ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎችን ወይም የአንድ ጎሳ አባላትን ብቻ ወስዶ ብሔር ማለት ትክክል አይደለም። ሌላው 'ብሔረሰብ' የሚለው ቃል ነው። 'ሰብ' የሚለው ቃል እንደዚሁ የግዕዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም 'ሰው' ማለት ነው። ስለዚህ ብሔረሰብ ማለት የአገር ልጅ (የወንዝ ልጅ) ማለት ነው።

ትንሽ ቀደም ያለው ትዉልድ ጠንቅቆ እንደሚያዉቀው የኢትዮጲያ ሕዝብ ከጣሊያን ወረራ በፊት ከኢትዮጵያዊነት ዝቅ ብሎ ማንነቱን መግለፅ ሲፈልግ ትግሬ (በከፊል አሁን ኤርትራና ትግራይ)፣ አክሱም፣ ጎንደሬ፣ ጎጃሜ፣ ወሎ፣ አርሲ፣ ወለጋ፣ ሐረርጌ፣ መንዜ፣ ወዘተ በማለት ከመጣበት ቦታ ወይም አልፎ አልፎ ከመተዳደሪያው አኳያ (ለምሳሌ አሁን ኦሮሞ የተባለዉ የሐረርጌ ገበሬ ራሱን 'ቆቱ' [አራሽ]

ብሎ ነበር የሚጠራው - የአሊ ቢራን የቀድሞ ቃለመጠይቅ ማድመጥ ይበቃል) ይናገራል እንጂ ጣሊያን ወይም የጣሊያን ባንዳ እና ዉላጆች በዚህ ዘመን እንዳመጡብን ራሱን ወይም ሌላዉን አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ አደሬ፣ ሺናሻ፣ ወዘተ... እያለ የጠራበት ቢጠራም ከሌላዉ የመለያ ምልክት ያደረገበት ወቅት የለም። በዚህ ዘመን የሰዉን ዘዉግ [ወይም በመንግስት ቋንቋ 'ብሔር'] ለመግለፅ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉት ስሞችም ቢሆን ትርጓሜአቸው ሆን ተብሎ ተዛብቶ ነዉ እንጂ ወይ ቋንቋን ወይ ስራን ወይ ደሞ ሃይማኖትን የሚገልፁ ናቸው። ቋንቋ ደግሞ የምትማረዉ እንጂ አብሮህ የሚወለድ አደለም። ሁላችንም እንደምናዉቀው ኢሕአዴግ ስልጣን ላይ እስከሚወጣ አማራ ማለት ክርስቲያን ማለት ነበር። ቀደም ሲል ደሞ አራሽ ማለት እንደነበር የፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ መፅሐፍ ይገልፃል። ኦሮሞ የሚለዉ ቃል አሁን ኦሮሞ ተብሎ የሚጠራው ህዝብ ከሚናገረዉ ቋንቋ ውስጥ ትርጉም አይገኝለትም [ቋንቋዉን በመጠኑም ቢሆን እናገራለሁ]። ይልቅ በቀደሙ የጀርመን ካህናት የተፃፉ ፅሁፎችን ማገላበጥ ብዙ ሊያስተምር ይችላል። ሌላዉንም ቢሆን አንደዚሁ ቀረብ አርገን ብናየዉ ሰዎችን ለመለያየት እንቅልፍ አጥተው የሚያድሩ ሰዎች አንደሚያስቡት ትርጉም የሚሰጥ ነገር የለዉም። አማራ ወይም ትግሬ ወይም ኦሮሞ የሚለው ቅፅል 'ዘር'ን ያመለክታል እያልን ከሆን ደማችን ቢመረመር በዚሁ መልኩ የሚከፋፍለን የዘረ-መል ስሪት 'genetic makeup' አለን ማለት ነዉ? እጅግ በጣም ብዙ ጥያቄዎችን መዘርዘር ይቻላል። የፈለገ ያህል ቢደከምም ቅሉ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ፣ አደሬ፣ ሺናሻ፣ ኤርትሬ ወይም ትግሬ የሚባል የሰዉ ዘር እኛ ካልፈጠርነዉ ሊገኝ አይችልም። የለምም!! ልክ ከፋፍሎ መግዛትን የግድ መጠቀም የነበረበት ጣልያን እንዳደረገዉ አንተ አማርኛ ስለተናገርክ እና ሰላም ስለነሳሽኝ አማራ ነህ፣ አንተ ደግሞ ሲዳምኛ ከሚናገሩ ሰዎች ጋር ስለሆንክ ሲዳማ ትባላለህ ወዘተ...ሊባል ይችላል። የፖለቲካ እና የፖለቲከኞች ሐቅ የሁላችንም ሐቅ ይሁን ካላልን በስተቀር ይህ በጭራሽ ከሰዉ ልጅ ማንነት ጋር የሚገናኝ ፅንሥ ሃሳብ አደለም።

የፖለቲከኞች ሐቅ የሁላችንም ሐቅ ይሁን **የሚሉ ሰዎች ካሉ የተወሰኑ ቀላል ጥያቄዎች አሉኝ**

1. **እነዚህ ብሄራት መቼ ተፈጠሩ** ማንስ ፈጠራቸው?
2. **አንድ ሰው ጉራጌ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ወላይታ ወይም ሌላ ለመሆን ምን ምን ማሟላት አለበት?**
3. ብሔር/ብሔረሰብ የሚለወጥ ነገር ነው ወይስ ለዘላለም ባላበት የሚቀጥል?
4. ኢትዮጵያ ዉስጥ ሁሉም ሰዉ የአንድ ብቻ ብሔር/ብሔረሰብ አባል እንዲሆን ይጠበቃል። ለምን?
5. ብሔር/ብሔረሰብ ምርጫ የማንነት ጉዳይ እንዲሆን ከተወሰነ ለምን እያንዳንዱ ግለሰብ በራሱ እንዲወስን አይፈቀድም?
6. እና ሌሎች....

**ከላይ እንደፃፍኩት ይህ ቅርጽ የለሽ እና ትርጉም አልባ ፅንስ ሃሳብ የመጣው የጣሊያን ፋሽስት ከፋፍሎ ለመግዛት ከጠነሰሰው ሴራ ነው።**

**እንግዲህ ህወሃት/ኢህአደግ ከመነሻው ለመከፋፈል እና ጠላትና ወዳጅ ለማበጀት የተጠቀመበት ይህ የተቀየደ ፅንሰ ሃሳብ ፋይዳ ቢስ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስረዳት ለቀባሪ ማርዳት ነው። ዋናው ጥያቄ ህወሃት/ኢህአዴግ ይህን የጅል ጨዋታ እስከመቼ ይዞ ይቀጥላል ነው። በርግጥ እሱን በስልጣን ላይ እስካቆየው ድረስ ብሎ ባጭሩ መመለስ ይቻል ይሆናል። ከዛ ባሻገር ግን እንደጠላት የሚቆጠሩትን አማራ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ን በጠላትነት እስካቆየለት ድረስ ኢህአዴግ ይህን የሞኝ ጅራፉን ይዞ እንደሚቆይ ምንም ጥርጥር የለውም።**

**የህወሃት መሪዎች ይህን ፅንሰ ሃሳብ ለዚህ ዓላማ መጠቀማቸው አይደለም ይህችን አገር አሁን ያለችበት ቦታ እንድትገኝ ያደረጋት። ይልቁንስ ይህን ግልብ አስተምህሮ እንደማይሻር ሃቅ አንግበው ለ27 ዓመታት ይህችን አገር ያመሱ አድርባዮችና መሃይም ሙሁራን ናቸው። እንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር እንግሊዛዊ እንደማያደርግ እያወቁ፣ ፈረንሳይኛ መናገር ፈረንሳዊ እንደማያደርግ እያወቁ፣ አረብኛ መናገር አረብኛ እንደማያደርግ እያወቁ፣ ትግሬኛ ቋንቋ ስለተናገሩ ትግሬ ነኝ ብለው ከበሮ የመቱ፣ ኦሮምኛ ስለተናገሩ ኦሮሞ ነኝ ብለው ጮቤ የረገጡ፣ አማርኛ ስለተናገሩ አማራ ነኝ ብለው አገር ይያዝ ያሉ፣ ወላይተኛ ስለተናገሩ ወላይታ ነኝ ብሎ ምድር የጠበበችወ፦ ወዘተ ነው ለህወሃት መሳሪያ ሆኖ ኢትዮጵያን የምታክል ታላቅ አገር ያዋረደው። የህወሃት ድንቁርና ብቻ ላለንበት ችግር እንደ ብቸኛ ምክንያት ሊጠቀስ አይችልም። እኔ ትግሬ ነኝ፣ እኔ ኦሮሞ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ፣ ወዘተ ስንል ነዉ ለህወሃት መሣሪያ የሆነው። ለእነሱ የአገር ማፍረስ አጀንዳ መሳሪያ የሆናቸዉ እኛው ነን። በጣት ከሚቆጠሩ አዋቂዎች በስተቀር እኔ ብሄሬ ኢትዮጵያ ነው ያለ ሰው ማግኘት አይቻልም። ይህ ያሳፍራል። ህወሃት ይህን ሁሉ ህዝብ እንዲህ እንደጎርፍ ውሃ ሲነዳው መኖሩ ያሳዝናል።**

**በ 5 ሺህ ዓመታት ልፋትና ድካም የተገነባችውን ታላቅ አገር የውርጋጥ መፈንጫ አደረግናት። እልፍ አዕላፋት የወደቁላትን ኢትዮጵያ የጎጠኞች እና የባንዳ ተላላኪዎች መጫወቻ አደረግናት። እንዴት አንድ ሰዉ ስሙና የተወለደበት ቦታ ታይቶ አንተ እንዲህ ነህ አንቺ እንዲያ ነሽ ይባላልላ የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው ለምሳሌ በእናቱ በኩል ያሉትን ሴት አያቶቹን እስከ ሰባት ትውልድ የሚቆጥረው ነው ወይስ ሰው ከአባቱና ከአባቱ አባት ብቻ ነው የሚወለደው? መቼም ይህ ታላቅ ህዝብ እንዲህ ገብስ የሆነበት ዘመን ያለ አይመስለኝም።**

ኢትዮጵያን መታደግ የምንፈልግ ከሆነ ይህን የጅል ጨዋታ ማቆም አለብን። ሰው መጀመሪያ ሰው ነው። ከዛ በኋላም ኢትዮጵያዊ ነው። የግድ ህወሃት የሰጠንን ማንነት መቀበል ያለብን አይመስለኝም። እንዴት ለማንም የባንዳ ዉላጅ ይህን ያህል ስልጣን እንሰጣለን? መቼም ይህ ነገር የገባችሁ ልታስረዱን እንደምትችሉ አምናለሁ።

፬. ከብሔር እና ብሄረሰብ ከሚለው የህወሃት/ኢህአዴግ ተረት ተረት አጠገብ በግልጽ እየታየ የመጣው ክስተት ይኸው ጎጥና ጎሳን መሰረት ያደረገ ወገንተኝነት ነው። በመጀመሪያዎቹ የህወሃት/ኢህአዴግ 14 የስልጣን ዓመታት በትግራይ ተወላጆች ዘንድ ህወሃትን በተመለከተ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ አመለካከት አልነበረም። የአድዋ አካባቢ ተወላጆች እጅግ ቅጥ ያጣ የህወሃት ደጋፊነት ይታይባቸው እንደነበር ግልጽ ነው። በርግጥ የሰሜን ትግራይ ልጆች የአድዋን እና የመቀሌን ተወላጆች መጤ የወታደር ልጆች በማለት እንደሚለዩአቸው ከአዲግራቱ ተወላጅ ወዳጄ ቀደም ብዬ ሰምቻለሁ።

የትግራይ ተወላጆች በ 'ትግሬ' ነት የህወሃት - ወደውም ሆነ በግድ - አምላኪ የሆኑት ከ1997 ምርጫ በኋላ ነው። ህዝብን ማስፈራራትና ህዝብን ከህዝብ ማጋጨት ከጣሊያን ፋሽስት ጌቶቹ የተማረዉ ህወሃት 'ኢንተር ሃምዌ' የሚል ዘፈን በመዝፈን ቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይን ተወላጅ ጠላት አድርጓል በሚል ፕሮፓጋንዳ ህዝቡን ከጀርባው ለማሰለፍ ቻለ። ይህ ማለት ግን የህወሃትን ተንኮል የትግራይ ተወላጅ በሙሉ አያውቅም ለማለት አይደለም። በርካታ ቱባ ምሁር እና ፖለቲከኛ የወጣበትን ምድር እንዲህ ልለው አይቻለኝም።

እጅግ የሚያሳዝነው ግን ስንት ጀግና የወጣበት ይህ ታላቅ ምድር የዚህ ፀረ ኢትዮጵያ እና ወሮበላ ድርጅት ከለላና መከታ መሆኑ ነው። እንደ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ በሚሊዮኖች የሚገመት የትግራይ ህዝብ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እንደሚኖር ጠንቅቄ አውቃለሁ። ያም ሆኖ ግን ባለፉት 40 ዓመት በተለፈፈበት ፕሮፓጋንዳ  እና ማስፈራራት ምክንያት ህወሃትን ከነጉድፉ ድርጅቴ ብሎ አቅፎ ይዞት ይኖራል። አሁን አሁንማ እንደ ቅዱስ ታቦት ህወሃትን የተዳፈረ ወይም በክፉ ያነሳ ውጉዝ ከመአርዮስ አይነት ዘመን ላይ ደርሰናል። ምክንያታዊ ውይይት ማድረግ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። አንድ ሰው ህወሃት/ኢህአዴግን በተመለከተ ለመናገር የተናጋሪው ማንነት መጀመሪያ መታወቅ አስፈላጊ እየሆነ ነው። 'አማራ' ውን ምቀኛ (ይህም ከጣሊያን ፋሽስት የተወሰደ ነው የሃበሻ ጀብዱን ያንብቡ) 'ኦሮሞ' ውን ጠባብ ወዘተ እያሉ ማሳነስና ማንቋሸሽ የተለመደ ሆኗል ። ምንም እንኳን የህወሃት መሪዎች የትግራይን ህዝብ የትግላቸው ጭዳ ለማድረግ ያልፈጠሩት ተረት እና ያልሰሩት ወንጀል ባይኖርም የትግራይ ህዝብ ግን በዚህ መጠን የህወሃት መሳሪያ መሆኑ ያስደንቃል።

በየመስሪያ ቤቱ ጉዳይ ለማስፈፀም መጥተው ህወሃት የሰጣቸውን 'ትግሬ' ነት እንደ መሳሪያ ሲጠቀሙበት ሌላው ህዝብ ምን እንደሚሰማው አያስቡም። ለምሳሌ በአገር ዉስጥ ገቢ መስሪያ ቤት ጉዳይ ሊያስፈጽሙ መጥተው ጭራሽ የመስሪያ ቤቱ አዛዥ ለመሆን ሲሞክሩ ትንሽ አያፍሩም። ዉልና ማስረጃ መጥተው እነሱ የመጡበት ጉዳይ በተፃፈም ይሁን ባልተፃፈ ህግ እንዲሰራላቸው ያዙኝ ልቀቁኝ ሲሉ ሰው ይታዘባል አይሉም። በጉምሩክ መስሪያ ቤት እና ግምጃ ቤቶች ከላይ እስከታች ተሰግስገው 'ትግሬ' ከሚሉት ዉጪ የሆነውን እንደጠላት ሲያጉላሉና ሲያዋክቡ ሰው እያያቸው እንደሆነ አያስተውሉም። ከየትም ሃገር ያመጡትና ሊቀረጥ የሚገባው ዕቃ በተለየ በር ወጥቶ ያለምንም ቀረጥ ሲጫንላቸው ደሃው ኢትዮጵያ ህዝብ ትዝ አይላቸውም። ህዝብ ተራ ጠብቆ የሚስተናገድባቸው ቦታዎች ላይ ሳይቀር እንደ ከብት ተራ ዘለዉ ሲሄዱ - በተለይ አዉሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች አካባቢ - እጅግ ያሳፍራሉ። በየቡና ቤቱ ገብተው እነርሱ ከሚፈልጉት ሰዉና መዚቃ ውጭ ማየትና መስማት ጠልተው ሲወላገዱ ይህ ቀን የሚያልፍ አይመስላቸውም። ሌላም ሌላም ማለት ይቻላል። ዋናው ቁም ነገር ግን ይህ ሁሉ ከትግራይ ህዝብ ባህልና ማንነት የማይመነጭ ህወሃትን እንደታቦት እና አምላክ መመኪያ ከማድረግ የመጣ ታላቅ ስህተት ነው። የትግራይ ህዝብ የኢትዮጵያ ምስረታ ላይ ትልቅ ሚና የተጫወተ እና አሁንም ሊጫወት የሚገባዉ ህዝብ ነው። ህወሃት ከትግራይ ህዝብ ሊወጣ ይችላል። የትግራይ ህዝበ ግን በምንም መልኩ የህወሃት ዉጤት ሊሆን አይችልም። አይገባምም።

በህዝብ የተከበሩ መንፈሳውያንና ምሁራን የትግራይን ህዝብ ከዚህ አሁን ካለበት ቅዠት እንዲወጣ ሊያግዙት ይገባል። ይህ ብዙ መስዋዕትነት ያስከፍል ይሆናል። ታላላቅ አባቶች/እናቶች እና ምሁራን ይህን  መስዋዕትነት ለመክፈል ካልተዘጋጁ ይህ ንፁህ እና ታላቅ የሆነ ህዝብ በህወሃት ስልታዊ የመነጠል አካሄድ ምክንያት እጅግ ሰፊና ጥልቅ መከራ ሊደርስበት ይችላል። አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ አባራ ያስነሰው የጥቂት 'ትግሬ' ዎች ህይወት መቀጠፍና የንብረት መውደም - የህወሃት የተደናቆረ ፖለቲካ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ - አድማሱን አስፍቶ የማይቀጥልበት ምክንያት ለኔ አይታየኝም። ህወሃት ጥቂት 'ትግሬ' ዎችን (በተለይ ደግሞ የአድዋ ተወላጆችን) ቅጥ ባጣ ዝርፊያና ሙስና አበልጽጎ ሊሆን ይችላል። ለትግራይ ህዝብም ቢሆን ከፍተኛ የሥራ ዕድል ፈጥሮ ሊሆን ይችላል። ኢፈርት እንዳለው ከሆነ ይህ ሁሉ ተደርጓል። ይደረግ። እንዲህ ያለ ቅጥ ያጣ በአንድ አካባቢ ላይ ያተኮረ ልማት እና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ግን ይህን የተለየ አካባቢም ሆነ አገራቱን አይጠቅምም። ብዙ የዋሃን የህወሃት ካድሬዎች እንደሚያስቡት ሳይሆን ትግራይ (በየትኛውም የድንበር ማዕቀፍ ውስጥ ሆና) በተዓምር ራሷን የቻለች አገር ሆና መኖር አትችልም።

ለዚህም የሚሆን ጂኦግራፊያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ገፅታ የላትም። አሁን ያለችበት የምጣኔ ሃብት ሁኔታም ቢሆን የእንቧይ ካብ ነው። ስለዚህ ትግራይ የኢትዮጵያ ቁልፍ አካል ሆና መቀጠሏ ስለማይቀር የትግራይ ህዝብ ህወሃትን እንደ ድፍርስ ወንዝ (አልፎ ሂያጅ ውሃ) እንጂ እንደ ኩሬ ባይመለከተው ጥሩ ነው። ህወሃት ያልፋል የትግራይ ህዝብ ግን ከሌሎች ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር ዘላለም ይኖራል። ይህ ግልጽ ሊሆን ካልቻለ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። ህወሃት የትግራይን ህዝብ ከምንም ሊያድነዉ አይችልም። ህዝብ እንጂ ህዝብን ሌላ ማንም ሊጠብቀው አይችልም። ህዝብ አንቅሮ ከተፋ ምን ሊያደርግ እንደሚችል የደርግን ታሪክ ባልተንሸዋረረ አይን መመልከት ነው። ስለሆነም ዘሬ ነገ ሳይል የትግራይ ህዝብ የሚነገረውንና እና የሚነዛለትን ዕለታዊ ፕሮፓጋንዳ ወደጎን በመተው ከብዙ መከራና ችግር የታደገውን የኢትዮጵያ ህዝብ በማገዝ ይህን የወመኔዎች ስብስብ የሆነ ድርጅት ከጉያው አዉጥቶ በመጣል እርኩስነቱን ሌላው እንደሚያየው ሊያይ ይገባል።

የትግራይ ህዝብ እንደ መለስ ዜናዊ ባለ ጋጠ ወጥና ፈሪ ሊወከል ወይም ሊሸፈን አይገባም። የነ ንጉሥ ኢዛና፣ የነ ንጉሥ ካሌብ፣ የነ አጼ ዮሃንስ፣ የነ እራስ አሉላ አባነጋ፣ እና የሌሎች በርካታ ጀግኖች አገር መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። ብዙ የሚጠራብቸው ጀግኖች ቢኖሩትም አሁንም ይህ እንደ ጥቁር ደመና እላዩ ላይ ያንዣበበውን የህወሃት ጠል ለማስወገድ ቆራጥ ልጆች ያስፈልጉታል። ይህን የሚያደርጉ ጀግኖች ትግራይ እንደምትወልድ ደግሞ የምናውቅ እናውቀዋለን።

፫. ህወሃት/ኢህአዴግ እጅግ የሚደንቅ የጊዜ አጋጣሚ አግኝቶ ምንም ሳይጠቀምበት ወይም ሳይጠቅምበት ያለፈ ጉደኛ የፖለቲካ ድርጅት ነው። የድርጅቱ ዋና ችግር ኋላቀርት፣ ንቅዘት፣ ዘገምተኝነትና እጅግ ያረጀ የፖለቲካ አመለካከት ማራመዱ እንዲሁም በጣም መሃይም እና ጎጠኛ በሆኑ ሽማግሌዎች መመራቱ ነው። የህወሃት መሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ እንደ ጠላት (ልክ እንደ ጣሊያን ፋሽስት) የሚያዩ መሆናቸዉን አይተናል። ወንድ ሴት ህፃን ሽማግሌ ሳይሉ የነሱን አመለካከት ወይም የነሱን ቅጥ ያጣ አገዛዝ የሚቃወም ወይም ለመጠየቅ የደፈረ ሁሉ ለነእርሱ ጠላት ነው ። መግደል ማስገደል፣ በሰዉ ልጅ ላይ እጅግ ዘግናኝ ጭካኔ መፈፀምና በሰዎች ስቃይና መከራ መደሰት የሚያረካቸዉ አረመኔዎች ናቸው። በኢትዮጵያውያን ውርደት የሚመፃደቁ ጉዶች ናቸው። የህወሃት መሪዎች እንደሰው ያስባሉ ብለው የቀረቧቸውንና ሊከራከሯቸው የሞከሩትን ወንዱንም ሴቱንም፣ አዋቂውንም ልጁንም በወሲብ ሲያነውሩ፣ በመርዝ ሲያሰቃዩ፣ ጭካኔ የተሞላበት ድብደባ ሲያካሂዱ፣ የሴት ብልት በእንጨት ሲጎረጉሩ፣ የወንድ ፊንጢጣ በእንጨት ሲቀዱ፣ የወንድ ብልት ሲቀጠቅጡ፣ ወንድንም ሴትንም እንደ እንስሳ በቡድን ሲደፍሩ፣ የሴት ጡት በምላጭ ሲተለትሉ፣ የእጅና የእግር ጥፍር ሲነቅሉ፣ እስረኛን በወንበዴ በጠባብ እስር ቤት ውስጥ ሲያስደበድቡ፣ ንፁሃንን ያሰሩበትን እስር ቤት በእሳት አንድደው ከነነፍሳቸው የሚያቃጥሉ፣ ኧረ ምኑ ቅጡ በግፍ ተወልደዉ በግፍ የኖሩ ናቸዉ። አንዳንዴ የጣሊያን ፋሽስት ያደረሰባቸዉን መከራ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየተወጡትም ይመስላል። በዚህ ጋጠ ወጥነታቸው ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ ተቀይሟቸዋል። አቂሟልም። አጋጣሚዉን እንዳገኘም ከመበቀል ወደኋላ እንደማይል እያየነው ያለነው ሁሉ በቂ ማስረጃ ነው። ይህ የኢትዮጵያዉያን ስሜት ከጋምቤላ እስከ ቶጎጫሌ፣ ከወልቃይት ጠገዴ እስከ ራያ /አላማጣን ጨምሮ/ ድረስ የታየ ነው። ዛሬ እጄ ላይ መሣሪያ አለኝ ብሎ በጉልበት ይህን ስሜት እና የስሜቱን ነፀብራቅ ለማፈን መሞከር - የህወሃት ድንቁርና ቢታወቅም - የሞኝ በትር ከመሆን አያልፍም።

ህወሃት ከዚህ በኋላ በዚህ ዓይነት ኋላቀር እና አረመኔያዊ መንገድ መቀጠል አይችልም። ከስብሃት ነጋ አንስቶ እስከ ታችኛው አቃጣሪ ካድሬ እስከ አሁን የሄዱበት መንገድ ገደል ጫፍ ላይ እንዳደረሳቸው ማወቅ አለባቸው። ውስጣቸው ያለዉ መሠረተ-ቢስ እና ከድንቁርና የመነጨ ጥላቻ ከውስጣቸው ሙሉ ለሙሉ መውጣት አለበት። እነርሱ ሊያወጡት ካልቻሉ የሚያወጣላቸው ሃይል ያስፈልጋል።

የህወሃት/ኢህአዴግ መሪዎችና አቃጣሪዎች ድርጅታቸው የሰጣቸወን ስብዕና ሳይሆን ፈጣሪ የሰጣቸውን ልቦና እና ጭንቅላት ተጠቅመው ቆም ብሎ ማሰብ ያስፈልጋቸዋል። ለ27 እና ከዛ በላይ ዓመታት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሠሩትን ሰይጣናዊ ግፍ አስበው ሊፀፀቱ ተፀፅተውም የኢትዮጵያን ህዝብ ከልብ ይቅርታ ሊጠይቁ ይገባል።

ህወሃት/ኢህአዴግን የሚያውቅ ሁሉ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ ከዚህ የደካሞች ድርጅት ሊጠበቅ የማይችል እንደሆነ ይረዳል። ትክክል ነዉ። ቢሆንም ግን እኔ እስከገባኝ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሰው እንዲያያቸውና እንዲምራቸው ከፈለጉ ህወሃቶች ከዚህ ውጭ ምንም አማራጭ የላቸውም። ይቅርታ መጠየቅ ብቻ አይደለም ከልብ የሆነ ይቅርታ ነው መጠየቅ ያለባቸው። ይህ ባይሆን ፀጉር ከምላሴ ይነቀል የኢትዮጵያ ህዝብ ህወሃትንና ቅጥያዎቹን ለአይን በሚቀፍ ለጆሮ በሚዘገንን መልኩ ይበቀላቸዋል። የሚያሳዝነው ከላይ እንዳልኩት ህወሃትን የሌላውን ህዝብ ያህል የሚፀየፈው ጨዋው የትግራይ ተወላጅ አብሮ የመከራው ሰለባ መሆኑ ነው። ቢያንስ ለዚህ ምስኪን ህዝብ ሲሉ እኚህ አረመኔ የህወሃት መሪዎች የልባቸውን ጥላሸት ሊያጥቡ ይገባል። ይህን ጥላሸት ሲያጥቡ ነው በዚህች አገር እና በየዋህ ህዝቧ ላይ ያደረሱትን መከራ እና ግፍ ሊረዱ የሚችሉት።

የሰሩት ግፍ አድማሱ እና ጥልቀቱ ሲገባቸው መቼም ሰው ናቸውና ይፀፀታሉ ብዬ እገምታለሁ። ሲፀፀቱም ይቅርታ ይጠይቃሉ። ይህን ቢያደርጉ ይድናሉ። ይህን ባያደርጉ ይጠፋሉ። አሁን በአገራችን እየተከሰተ ያለው የዚህ ጅማሮ መሆኑ ካልገባቸው ውርድ ከራሳቸው።

፮. ለማጠቃለል ያህል ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ምናልባት በአለም ላይ ካየኋቸው አገሮችና ዜጎቻቸው በተለየ መልኩ ቀና የሆኑ እና ፈሪሃ እግዚአብሄር ያላቸው ቢሆኑም ባለፉት 40 ዓመታት ውስጥ ከማንም እና ከምንም የባሰ መከራ ውስጥ ሲዳክሩ ይታያል። በየወቅቱ የተከሰቱ የገዢ  መዶቦች ዋናውን ድርሻ  ይወስዱ ይሆናል። ቢሆንም ግን ህዝቡ በክፉ እና አረመኔ ገዚዎች ስር በተለያዩ ምክንያቶች አጎንብሶ መኖሩ ግን የዛኑ ያህል ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እንደ ፖለቲካ (ለዛውም በጥላቻ ላይ የተመሰረተ) ሸቀጥ የሚጠቀም እና አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ ደግሞ እንደ መስጊድ ውሻ መድረሻ የሚያሳጣ እጅግ ባለጌ የሆኑ ሰዎች ተሰባስበው ራሱ ላይ ሲቀመጡበት እግዚአብሄር ንጉስን ይሾማል በሚል የዋህነት አጎንብሶ የሚገዛ ህዝብ ከጠያቂነት ሊድን የሚችል አይመስለኝም። በርግጥ ከታሰበለት የእርስ በርስ መጨራረስ አጀንዳ ራሱን ጠብቆ ኢትዮጵያ እንደ አገር እንድትቀጥል ስላደረገ የኢትዮጵያን ህዝብ ማክበርና ማወደስ ያስፈልጋል። ባለችኝ ትንሽ አቅም ለኢትዮጵያውያን ጎንበስ ብዬ እጅ እንድነሳ ይፈቀድልኝ።

ግን ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ያለው ጀግንነት እና ያለው ብስለት ኢትዮጵያን እንደ አገር ከማቆየት ያለፈ ትልቅ ጉልበት ሊሆነዉ ይገባል። ይህን የሚያውቅ እና አሁን የጎንደር፣ የአምቦ፣ የወልዲያ ፣ እና የሌሎችም ወጣቶች እነ ለማ መገርሣ፣ ገዱ አንዳርጋቸው፣ ታማኝ በየነ፣ ቴድሮስ ካሳሁን፣ ሃጫሉ ሁንዴሳ ወዘተ የመሳለሉት ግለሰቦች በቡድን እና በተናጠል የሚያደርጉት ትግል ምን ያህል ታዕምር እንደፈጠረና እየፈጠረም እንደሆነ የሚያይ ምን ለማለት እንደፈለኩ ይገባዋል። እኛ ኢትዮጵያውያን ለብልግና እና ጋጠ ወጥነት ቦታ የለንም። በቋንቋው እና በተሰጠው የጎሳ ስም ምክንያት ለፍቶ አዳሪ የሆነ ደሃ ህዝብ እንደ ሽንኩርት ሲከተፍ ዝም ብሎ የሚያይ ኢትዮጵያዊ የዚህች ቅዱስ ምድር ዜጋ ሊሆን አይችልም። ይህን ክፉ ስራ እንዲሰራ የሚያደርጉት ታዘው የሚሰሩትን ሁሉ ተገቢውን ቅጣት ለመስጠት ችሎታውም ጉልበቱም ያለው ህዝብ ነውና ዝም ማለቱ ነው ብዙም ለተመልካች ግልጽ የማይሆነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ኢትዮጵያዊነቱን ማንም እንዳልሰጠው ሁሉ ማንም አይነሳውም። የኢትዮጵያ ህዝብ ለብዙ ሺህ ዓመታት ተከባብሮና ተዋዶ፣ ተዋልዶና ተሳስሮ የኖረ እንደመሆኑ ማንም ጎጠኛ መጥቶ በቋንቋና በመንደር ሊከፋፍለው እንደማይችል ሊያውቅ ይገባል።

ህወሃት/ኢህአዴግ ሲቋቋም ጀምሮ በደካማ ግለሰቦችና በደካማ አስተሳሰብ ላይ የተመሠረት እንደመሆኑ ለኢትዮጵያ አና ለኢትዮጵያውያን አይመጥንም። ይህን ድርጅት የኢትዮጵያ ህዝብ ጨዋ ስለሆነ ይህን ያህል ታግሷል እንበል። ከዚህ በኋላ ግን ይህንን ባንዳ ድርጅት ለመታገሥ ምንም ምክንያት ያለን አይመስለኝም። ይህ የገብጋቦች ድርጅት ትግሉን እና ታጋዮችን ለመወንጀል እንደማይተኛ ግልፅ ነው፡፡ ህወሃት/ኢህአዴግ ግን ሌሎች አካላትን ፀረ-ሰላም ናቸው ብሎ ለመተቸት ምንም የሞራል ብቃት የለዉም። ህወሃት/ኢህአዴግ የትኛዉንም አካል አገር በመዝረፍና ታሪክ በማንቋሸሽ ሊወቅስ አይችለም። ህወሃት/ኢህአዴግ ማንኛዉንም አካል በጋጠ ወጥነትና በሥርዓት አልበኝነት ሊወቅስ የሚችልበት ብቃቱ የለዉም። ህወሃት/ኢህአዴግ የትኛዉንም አካል በአሸባሪነትና በፀብ አጫሪነት ሊወቅስ የሚችልበት አቅምም ሆነ ሞራል የለዉም። ህወሃት/ኢህአዴግ ማንኛዉንም አካል ከሃቅ እና ከእዉነት በመሸሽ ወይም ዉሸትን በማምለክ ለመዉቀስ የሚችለበት ሞራል የለዉም። ባጠቃላይ ህወሃት/ኢህአዴግ በድርጅታዊ ዝቅጠት በኢትዮጵያ ምድር ከተከሰቱ አካላት ሁሉ በጣም አሳፋሪ ደረጃ የደረሰ ከዚህም የባሰ ዉርደት ዉስጥ ሊገባ የሚችል የመሀይማን ስብስብ ነዉ። ከዚህ ድርጅት የኢትዮጲያ ሕዝብ በየዋህነት መልካም አስተዳደርና ፍትህ መጠበቁ እንደ ሕዝብ የሰራዉ የመጨረሻ ትልቁ ታሪካዊ ስህተት እንደሚሆን ጥርጥር የለኝም።

እነዚህ ባንዳ የባንዳ ልጆችም ከልብ ተፀፅተው ይቅርታ የሚጠይቁ ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ በጨዋ ደንብ ይዳኛቸው ዘንድ ምኞቴ ነው። አሁን በላቸው ትዕቢትና ጋጠ ወጥነት የሚቀጥሉ ከሆነ ግን ወንድ ሴት፣ ህፃን አዋቂ ሳንል ይህችን አገር ከነዚህ ቁሻሻዎች ማፅዳት ይኖርብናል። ኢትዮጵያን ያክል አገር እንዲህ ባለ የግፍና መከራ አረንቋ ውስጥ ስትዳክር ዝም ብለን ማየታችን ያለብንን የታሪክ አደራ አለመረዳት ነው። ከውጭ ጠላት ነፍሳቸውን ሰውተው የጠበቁን አባቶቻችንና እናቶቻችን ከዚህ ዓይነት የውስጥ ጠላት አገራችንን መጠበቅ አለመቻላችን ምን ያህል እንደሚያሳዝናቸው መገመት ቀላል ነዉ። እንዴት ኢትዮጵያ ሃገራችንን ከተራ የወንበዴ ቡድን መጠበቅ አቃተን ጎበዝ? ግን እኛ ኢትዮጵያውያን ይህን ያህል ፈሪ ነን እንዴ? የመይሳው ካሳ፣ የገብርዬ፣ የአሉላ አባ ነጋ፣ የእምዬ ሚኒሊክ፣ የባልቻ አባ ነፍሶ፣ የበላይ ዘለቀ፣ የሺህ ጀግኖች ልጆች አይደለንም እንዴ? ምን እየጠበቅን ነው?